# ሁለተኛ  ዙር የቁርኝት መርሃ ግብር ስምምነት ተፈረመ

አዲስ አበባ ግንቦት 2007፡ የኢትዮጵያ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከህንዶቹ ማዕከላዊ የቆዳ ምርምር ኢንስቲትዩት እና ከጫማ ዲዛይን እና ልማት ኢንስቲትዩት ጋር የሁለት ዓመታት የቁርኝት መርሃ ግብር ስምምነት ተፈራረመ፡፡





አዲሱ ስምምነት ቀደም ብሎ ለሶስት ዓመታት የተካሄደዉ መርሃ ግብር ቀጣይ ሲሆን በዋነኛነት ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ባላቸዉ ተግባራት ላይ አተኩሮ እንደሚንቀሳቀስ ነዉ የተጠቆመዉ፡፡ ስምምነቱም ቅዳሜ ግንቦት 8 ቀን 2007 ዓ.ም የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ደኤታዉ አቶ ታደሰ ሀይሌ በተገኙበት በተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮች ተፈርሟል፡፡

2 ነጥብ 9 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ በጀት የተያዘለት ይህ 2ኛዉ ዙር የቁርኝት መርሃ ግብር በጥናትና ምርምር፣በትምህርትና ስልጠና በተለይም በከፍተኛ ትምህርት መስክና በሌሎች የእሴት ጭማሪ ባላቸዉ ተግባራት ዙሪያ አተኩሮ እንደሚከናወንም ነዉ የኢንስቲትዩቱ የእቅድና መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ብርሃኑ ያስታወቁት፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ 2ኛዉ ዙር የቁርኝት መርሃ ግብር ኢንስቲተዩቱ በከፍተኛ ደረጃ በሁለተኛና በዶክትሬት ድግሪ ደረጃ በሰለጠኑ ባለሞያዎች እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

ፕሮግራሙ ሀገሪቱ በንዑስ ዘርፉ ያቀደችዉን እቅድ እንድታሳካ ከማድረጉም በተጨማሪ ኢንስቲትዩቱ ለኢንዱስትሪዉ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ድጋፍ እንዲሰጥ ያስችለዋል ሲሉ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ